1

ታጋቹ ፖ ለቲከኛ

አዲስ ቶልቻ 05/20/13

በኢፌዴሪ የመንግስት ስርዓት ውስጥ በተለይ በግል የትምህርት ዘርፍ ቀደምት ስኬታማ

ኢንቨስተርና ባለሀብት ለመሆን የበቁት ዶ/ር ፍሰ ሃ እሸቱ ፣ ስ ኬታቸውንና አገራቸውን

ጣጥለው ወደ አሜሪ ካ ኮብልለው ውሉ የማይታወቅ ከህልም ዓለም የማይለይ ፖለቲካ

መዘባረቅ ከጀመሩ እነሆ አንደ ዓመት ሊሞላ ነው።

ዶ/ር ፍስሃ 80ዎቹ አጋማሽ ላይ ፒያሳ አካባቢ በአንድ ክፍል ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ

የአጭር ግዜ ስልጠና የሚሰጥ ትምህርት ቤት ነበራቸው፡፡ ከዚህ ተነስተው አስር ዓመት

በማይሞላ ግዜ ውስጥ በአገሪቱ የግል ከፍተኛ ትምህ ርት ታሪክ ውስጥ ቀደምትና ትልቅ

የሆነ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ባለቤትና ፕሬዚዳንት ለመሆን በቅተው እንደነበረ ይታወቃል ፤ ዩኒቲ

ዩኒቨ ርሲቲ ኮሌጅ።

ይህ ስኬታቸው ከቁሳዊ ጥቅም በተጨማሪ ዝናን አትርፎላቸው ነበር። እንደአገርም በአገሪቱ

የከፍተኛ ትምህርት አቅርቦት ላይ ለነበረ ው ችግር በመጠ ኑም ቢሆን ማስተንፈሻ ማበጀት

በመቻላቸው ጀግና የሚያስ ብል የዜግነት ኃላፊነት ተወጥተዋል። በርካታ ተመሳሳይ የግል

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲመሰ ርቱ አርአያ ሆነዋል።

ይሁን እንጂ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በአገራቸው የሰሩትንና ያገኙት ክብርና ዝና በዜሮ

አባዝተው፣ በውጭ ሃገረ በቅዠት አለም ውስጥ የሚኖሩ እንደነ ታማኝ በየነን የመሳሰሉ

ሰዎ ችን ጎራ ተቀላቅለዋል። አሁን ዶ/ር ፍስ ሃ አገር ቤት እያሉ እንዳደረጉት፣ለእርሳቸውም

ለአገርም የሚጠቅም ተጨባጭ ሰራ የሚሰሩ ሰ ው አይደሉም። የኢትዮጵያን ህዝብ ፍ ላጎትና

ፍቃድ የሌለው ያህል ቆጥረው መንግስት ገልብጬ አዲስ መንግስት እመሰርታለሁ የሚል

ቅዠት ውስጥ ናቸው ።

ዶ/ር ፍስሃን ከዕውኑ አለም ድንገት ወደቅዠቱ መሻገራቸው ብዙዎችን “የት ይደርሳል

የተባ ለ ጥጃ ሉ ካንዳ ቤት ተገኘ” አስብሏል፤ አሳዝኗል፣አስገርሟል። እርግጥ እጅግ በርካታ

2

ኢትዮጵያውያን በወጭ አገር የሚኖሩ የኢትዮጵያ ተቆርቋሪ ነን የሚሉ ሰዎ ችን ቅዠት

አይሰሙም፤ ቢሰ ሙም ከቁምነገር አይፅፉትም።

ዶ/ር ፍሰሃን ያሰታወሰኝ በቅርቡ ዕንቁ የተባለ በአማርኛ ቋንቋ የሚታተም ወርሃዊ መዕሄት

በግንቦት እትሙ ላ ይ የት አግኝቶ እዳና ጋራቸወ ባይገልፅም “ከዶ/ረ ፍስ ሃ እሸቱ ጋር

የተደረገ ቃለ መጠይቅ ” ብሎ ሰውየው ያወሩትን አስነብቦናል ፡፡ ሰውየው ያወሩት ነገር

የማይረ ባና የቅዠ ት ዓለም ውስጥ መኖራቸውን የሚያሳብቅ ቢሆንም፣ ቢያንስ ለአገር

ውስጥ አንባቢዎች ስ ለቀረበ ከዝብርቅርቁ ውስጥ በተወሰኑት ሃሳቦ ች ላ ይ አስተያየት ልሰጥ

ወድጄአለሁ።

ዕንቁ መፅሄት ዶ/ር ፍሰሃን ማነጋገር የጀመረው ዩኒቨርስቲዎ ን ሳይፈልጉ በመንገሰት ጫና

ነው የሸጡት ይባላል፣ እውነቱ ን ንገሩን በሚል ጥያቄ ነበር ።

ዶ/ር ፍስሃ ለጥያቄው ምላሽ መስ ጠ ት የጀመሩት ዕውነቱን በመና ገር ነበር፡፡ “መንግስት

አስገድዶኝ አይደለም የሸጥኩት” ብለዋል፡፡ ይህን ሊደብቁት የማይችሉት ዕውነት ስለሆነ

ሊዋሹ አይችሉም። ሆኖም ይህ ዕውነተኛ መልሳቸው “አገር ውስጥ በደል ስለደረሰ ብኝ ነው

የወጣሁት” የሚለውን ወደ ቅዠት የፖለቲካ ዓ ለም የገቡበትን ምክንያት ፉርሽ

ስለሚያደርገው፤ “በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳልሰራ ብዙ ሁኔታዎች ነበሩብኝ” ብለዋል።

እዚህ ላ ይ “በተዘዋዋሪ የደረ ሰ ብዎ ጫና ምንድነው?” የሚለውን ጥያቄ ጋዜጠኛው ማቅረብ

አልፈ ቀ ደም፡፡ ይህም ጋዜጠኛው እውነት ፈ ርጦ እንዲወጣ ከማድረግ ይልቅ የዶ/ር ፍስሃ

መደገፊያ የሌለው “ተበድያለሁ” የሚል በውጭ አገር ከተሞች በመሸጉ ስ ራ ፈት

ፖለቲከኞች ነን ባ ዮች ዘንድ የተለመደ ጩኸት ብቻ እንዲሰማ ያለውን ፍላ ጎት ያሳያል።

ያም ሆኖ ዶ/ር ፍስሃ “ተዘዋዋሪ” ያሉትን ጫና “አገራዊ ባለሀብቱና ስራ ፈጣሪውን

መደገፍና ማሳደግ ሲቻል የነበረው ሁኔታ በተቃራኒ ው ተፍጨርጭ ረው ያደጉትን

ባለሀብቶችና ተቋማት በአጓጉል ህጎች ማዳከም ስለሆነ ስ ራዬን መቀጠል ከማልችልበት

ደረ ጃ ላ ይ ደረ ስ ኩ” ሲሉ ገልፀውታል።

የግል ከፍተኛ የትምህ ርት ተቋማት በአግባቡ እንዳይንቀሳቀሱ ያሰረው የትኛው ህ ግ ፣ ደንብ

ወይም መመሪ ያ እንደሆነ ግን መና ገር አልደፈ ሩም።

3

እኛ ኢትዮጵያ ውስጥ የምንኖር ዜጎች የምናውቀው ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በ1980ዎ ቹ አጋማሽ ላይ በአንድ ክፍል ውስጥ ተማሪ ዎችን አንግሊዝኛ ቋንቋ የአጭ ር ጊዜ ስልጠና

ይሰጥ የነበረው ዩኒቲ የቋንቋ ትምህርት ቤት አስር አመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የራሱ ግዙፍ ካምፓስ ያለው፣ በአስራዎቹ ሺሆች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ተቀብሎ እስከ ሁለተኛ

ዲግሪ ድረስ የሚያሰ ለጥን ዩኒቨ ርስ ቲ ኮ ሌጅ ባለቤት ለመሆን መብቃታቸውን ነው።

ይህ በንግድ ስራ ውስጥ ድንቅ ሊባ ል የሚችል የዶ/ር ፍሰሃ እድገት፣ መንግስት አመቺ ፖሊሲዎ ቸን በማውጣት በተፈጠረ ምቹ ሁኔታ የተገኘ መሆኑም እርግጥ ነው። ገርጂ

የሚገኘውን ግዙፍ ካምፓስ የገነቡበት ን መሬት በምን አኳኋን ይሆን ያገኙት ? ዶ/ር ፍስሃ
በደርግ የመንግስት ሰ ርዓት ይህን ማድረ ግ አ ይችሉ እንደነበረ አያውቁም ይሆን ?

ሌላው እኛ ኢትዮጵያ ውስጥ የምንኖር ዜጎች የምና ውቀው ዶ/ር ፍስሃ አስር አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ የመንግስት ድጋፍ አስር ሺህ ብር ከማይሞላ ካፒታል ተነስ ተው በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደሚሊየርነት መለወጣቸውን ነው። ይህ አገር የሚያውቀ ው ፀሃይ የሞቀው እውነት ቢሆንም የግል ጉዳይ ስለሆነ ዝርዝ ር ጉዳይ ውስጥ መግባቱ አስፈላጊ አይደለም።

ያም ሆነ ይህ ዩኒቨርስቲውን የሸጡት በግል አመላቸው ከገቡበት አጣብቂኝ ለመውጣት

ነው፡፡ ዩኒቨ ርስቲውን ሽጠ ው እዳቸውን ከፋፍለው የተረፋ ቸውን ዱባይ ሄደው እንደዓለማችን የናጠጡ ቱ ጃሮ ች ቅንጡ የመዝናኛ ጀልባ ገዝተው አለቅጥ ሲዝና ኑበት እንደነበር ይነገራል።

ወደአሜሪካ ያቀኑት ከዚህ በኋላ ነው። ወደአሜሪ ካ ያደረ ጉትን ጉዞ አስመልከቶ ለእንቁ መፅሄት ሲናገሩ፣ “ከአገሬ እንደወጣሁ ወደ ዱባይ ነበር የሄድኩት፤ከዛ ወደ አሜሪ ካ ሄድኩ። በፖለቲካው ዓለም የረጅም ጊዜ ልምድ ካላቸው አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጋር

ከተመካከርን በኋላ ነው የሽግግር ምክር ቤት ለማቋቋም ውሳኔ ላይ የደረስነው፡፡ ኢትዮጵያ

ውስጥ ባለው የፍትህ እጦትና ጭቆና ምክን ያት ህዝቡ ይሰ ደዳ ል። ይህ ግን አንድ ቦታ ላይ መቆም አለበት ብለዋል፡፡”

ቀደም ሲል እንደጠቀ ስኩት ደ/ር ፍሰ ሃ ወደወጭ አገር የኮበለሉት በራሳቸው ችግር መሆኑን የኢትዮጵ ያ ህ ዝብ ያውቀዋል። ውጭ አገር ሲሄዱ፣ በአገር ቤት በነበረው ምቹ ሁኔታና በመንግስት ድጋፍ ባ ገኙት ስኬት ስ ማቸው ገንኖ ስለነበረ፣ በውጭ አገር የሚኖሩ እርሳቸው

4

“አገር ወዳድ” ያሉዋቸው፤ በትክክል ግን የኢትዮጵ ያ ህዝብ ገድሎ የቀበራቸውን ስርአቶች

የሚና ፍቁ ፣ ለኢትዮጵ ያ ህ ዝብ ደንታ የሌላቸው፣ እነርሱ የሚናፍቁት ስርአት ካልመጣ

ኢትዮጵያ እንድትጠፋ የሚመኙ፣ ላለፉት ሃያ አመታት ሲለፈልፉ የኖሩና በአገር ቤትም

በውጭም የተሰለቹ ግለሰቦች በአዲስ ምላስ አሮጌ ወሬያቸውን እንዲያወሩላቸው

ጠይቀዋቸው እርሳቸውም ተስማሙ።

እርግጥ ዶ/ር ፈ ሰሃ በአገር ቤት አፍርተውት የነበረውን ዝናና ሃ ብት አዝረክርከው ስ ለወጡ ፣

እጅ እጅ ያሉት ዲያስ ፖራ ፖለቲከኞች አዲስ ምላስ እንዲሆኑላ ቸው ሲጠይቋቸው እምቢ

ማለት የማይችሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ዛፍ ያጣ ጉሬዛ ሆነው በሚዋልሉ በት አገር ፣

የቀረ በላቸውን ጥያቄ አልቀበል ቢሉ እንደተለመደው “ወያኔ ሆዳም ምንትስ ፣ ቅብርጥስ

….” እያሉ እየተቀ ባበሉ ሻይ ለመጠጣት የሚያርፉበት ቦታ እስኪ ያጡ የሚከፍቱባቸውን

የማጥላላት ዘመቻ መቋቋም የሚችል የሞራል ጥንካሬ የላቸውም። ስ ለዚህ ምላሳቸውን

አዋሱዋቸው፤ የሽግግር ምክር ቤት በሚል ባዶ ነገር የታጀለ አሮጌ ወሬያቸውን ሊያወሩ።

ዶ/ር ፍስሃ “ኢትዮጵያ በብዛት ወደአገር ቤት ውስጥ ባ ለው የፍትህ እጦትና ጭቆና

ምክንያት ህዝቡ ይሰ ደዳል፣ ኢትዮጵያ ልጆቻ ን እያጣች ነው፣ ሰው እየሸሸ ነው ” ብለዋል።

እውነቱ ን ግን ከዚህ የተለየ ነው። በውጭ አገራት ለበርካታ አመታት ኖረው እውቀ ትና

ሃብት ያካበቱ ብዙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደአገር ቤት ተመልሰው

እየሰሩ ነው። በእርግጥ ወደአገር ቤት ለመመለስ የራሳቸው ችግር አለያም የሕ ዝብና የሕ ግ

ተጠ ያቂነት ያለባቸው በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች የትም እንደማይደርሱ ሆዳቸወ እያወቀ

“መንግስት ተገልበጦ፣ ሕዘባዊ ንቅናቄ፣ የአረ ብ አቢዮት ምንትስ ቅ ብርጥስ” እያሉ

ከሚያደናግሩዋቸው ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ላይ የእለት ኑሮ አቸውን

ለመደጎም ገንዘብ እየቃረሙ የሚኖሩና ራሳቸውን በሥራ ለመለወጥ ፍላጎቱና ተነሳሽነቱ

የሌላቸው እንዲሁም በግርግር በሚፈጠር የመድፌ ቀዳዳ ያህል አጋጣሚ ሥልጣን

እና ገኛለን ብለው የሚቋምጡ ጥቂ ት ሥራ ፈ ቶችና በምሁር ካባ የተጀቦ ኑ የወሬ ቋት

ዲያስፖራዎች ናቸው።

እርግጥ በኢፌዴሪ ህገመንግስት የዜጎች በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት ያለአንዳች ገደብ

ስለተከበረ ፣ ፓስፖርት አውጥ ተው ለተለያዩ ጉዳዮች ማለትም

ለትምህ ርት፣ለሥራ፣ለጉብኝትና ቤተሰ ብ ጥየቃ፣ለከፍተኛ ህ ክምና ፣እዚያው ለመኖር ወዘተ

ወደውጭ አገራት የሚጓዙ ኢትዮጵ ያውያን ቁጥር በደርግ የስልጣን ዘመን ከነበረው በእጅጉ

ጨምሯል፡፡ ይህ ግን ከመብት መከበር የመነጨ እንጂ የመብት ጥሰት ውጤት አይደለም።

5

ዕንቁ መፅሄት “ህገመንግስታዊ ስርዓቱ ን አክብረው በአገር ቤ ት በመታገል ችግሩን መፍታት

አይቻልም ነበር ወይ?” ሲል ለዶ/ር ፍስሃ ጥያቄ አቅርቧል። ዶ/ሩም ሲመልሱ

“እንደሚያስሩኝ ስለማውቅ ነው። ቢዝነስ የምትሰራ ከሆንክ ብዙ ነገር ይቆፍሩብሃል። አገር

ቤት በአንድ በኩል ቢዝነስ እየሰራህ በተቃውሞ ፖለቲካ ውጤታማ መሆን አይቻልም፡፡

የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ካልገባ ህ ደግሞ ጠንካራ ጉዳዮች አንስተህ መታገል አትችልም።

አገር ውስጥ መንግስት መቀየር አለበት ብለህ መከራከር አይቻልም። ” ብለዋል።

ዶ/ ር ፍስሃ “አገር ውስጥ ተቃዋሚ ፖለቲከኛ ያልሆንኩት እንደምታሰር ስለማውቅ ነው ”

ብለዋል። በአገር ቤት ተቃዋሚ ፖለቲከ ኛ መሆን ማለት በሚገኘው አጋጣሚ ሁሉ

መንግስትን በኃይልና በአመጽ ለ መለወጥ መስራት ማለት እንደሆነ በይ ፋ እስ ከመናገር

የዘለቀ ተገቢ ያልሆነ አካሄድ እየተከተሉ ለመሆኑ የዶ/ፍ ፍሰሃ አባባል በግልጽ ያሳየናል።

አገር ውስጥ እኮ በርካታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎ ች ሕጋዊ እውቅና አግኝተው

እየተንቀሳቀሱ መሆና ቸውን ሁሉ ሊክዱ መከጀላቸው በእጅጉ አስገራሚ ነው። መንግስት

ሕግና ሥርአት አክብረውና ሕ ገመንግሥታዊ ና ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ተጠቅመው

እየተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮ ችን፣አባ ላቱንና ደጋፊዎቻቸው ን

አላሰረም ፣ይህ ን ማድረ ግ የሚያስ ችለው አንዳችም የሕ ግ መሰረት የለውም ። ከዚህ ይልቅ

ምንም እንኳ አንዳንዶች አካሄዳቸው ህገወጥ ቢሆንም በሆደሰፊነት፣ ከዛሬ ነገ ይቃኑ

ይሆናል በሚል ታግሷቸዋል። እናም ዶ/ር ፍሰሃ በአገር ቤት ተቃዋሚ ፖለቲከኛ ቢሆኑ ም

እንኳ እንደማይታሰሩ ከውስጣቸው ያወቁታል፡፡ ይህ ማለት ግን ማንም ህ ገወጥ ነትን

ወደተግባ ር ለመለወጥ ሲሞክር መንግሥት ዝ ም በሎ ያያል ማለት አይደለም።

ህ ገመንግስቱን የማስከበር ከህዝ ብ የተሰጠው ኃላፊነት ስላለበት ሕግ የሚያዘውን ከማድረግ

እንደማይቆጠብ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባ ል። ሕ ግን ማክበርና ማስከበር ደግሞ የማንኛውም

በሕ ዝብ የተመረጠ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሊከተለው የሚገባ ቀዳሚ የአሰራር መርህ

ነው።

ዶ/ር ፍስሃ በዲያስ ፖራ የቅ ዠ ት ፖለቲከኞች ዘንድ እንደተለመደው ሁሉ ህገወጥ

እንቅስቃሴንና ዴሞክራሲያዊ መብትን ሳይለዩ ነው የዛበረቁት። በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ

አገር ሰዎች ህግ የመጣስ መብት የላቸውም። ፖለቲከኞችም እንደማንኛውም ዜጋ በህ ግ

አጥር ውስጥ ነው መንቀ ሳቀስ ያለባቸው። ህገወጥ ድርጊት የመፈፀም ዴሞክራሲያዊ

መብት የለም። ስለዚህ ዶ/ር ፍስ ሃም ህ ግ እስ ካከበሩ ድረስ በአገር ውስጥ በግልም ሆነ

6

በፓርቲ ተደራጅተው ተቃዋሚ ፖለቲከኛ የመሆን መብት ነበራቸ ው። እንደምታሰር

ስለማውቅ ነው የወጣሁት ያሉ ት ከእውነታው የተፋታ የበሬ ወለደ ማደናገሪ ያ ነው ፡፡

ዶ/ር ፍሰሃ “ኢትዮጵያ ውስጥ ቢዝነስና ፖለቲካን አብሮ ማስኬድም አይቻልም ” ብለዋል።

እርግጥ ቢዝነስም፣ ፖለቲካም ጥ ልቅ ትኩረትና ጥሞና የሚፈ ልጉ የሙሉ ጊዜ ስራዎች

በመሆና ቸወ ሁለቱን አጣምሮ መስ ራት ለአንዳንዶች አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። አቅሙ

አለን ያሉ ብዙ ተቃ ዋሚ ፖለቲከኞች ግን ይህን እያደረ ጉ ይገኛሉ። ባለፀጋ ነጋዴ የሆኑትን

የመኢአድ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ኃይሉ ሻውል፣ ሰ ሞኑን በአንድነት ውስጥ ውዝግብ ያስነሱ ት

ኢ/ር ዘለቀ ረዲ ከብዙዎቹ ነጋዴ ፖለቲከኞች መሃከል ሊጠ ቀሱ ይችላሉ።

ዶ/ር ፍስሃ “አገር ውስጥ መንግስ ት መቀየር አለበት ብሎ ማውራት አይቻ ልም”

ብለውናል። ህገመንግስቱ በሚፈ ደው መሰ ረት በምርጫ በሚገኝ የህዝብ የስልጣን ውክልና

ስልጣን እይዛለሁ ብሎ ከማውራትም በላይ በተግባር ይህን ማድረ ግ ይቻላል፡፡ ከዚህ ው ጭ

በኃይል መንግስት እለውጣለሁ ማለትና ለዚህ መንቀሳቀስ ግን በህ ግ ያስጠ ይቃል፡፡ ያም

ሆኖ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት መንግስትን ከምርጫ ውጭ ለመገልበጥ ያለ ፍላጎት በይፋ

ሲገለጽ ይሰማል፡፡ ምናልባት መንግስትን ከምርጫ ወጭ በኃይል እንገለብጣለን እየተባ ለ

በይፋ የሚፎ ከርበት አገር ኢትዮጵ ያ ብቻ ሳትሆን አትቀርም የሚል ግምት አለኝ ። ዶ/ር

ፍሰሃ እርስዎ አሜሪካዊ ቢሆኑና እዚያው አደባባይ ቆመው ለአሜሪካውያን “ጎበዝ ይህን

መንግስት በኃይልና በሁከት እንናደው!” ብለው ቢፎክሩና ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረ ግ

ቢንቀሳቀሱ የአሜሪ ካ መንግስት ሕ ግ የሚለቅዎ ይመስልዎ ታል?

የመንግስት ስልጣን እንዴት እንደሚያዝ የሚደነግግ ህገመንገስት ባ ለበት አገር መንግስትን

ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ መለወጥ አይቻልም። የኢትዮጵያ ህገመንግስትም ይህን ይላል።

በዚህ የህገመንግስቱ ድንጋጌ መሰረት መንግሰትን የመለወጥና የመሰ የም መብት፣ ያለው

ብቸኛው የመንግሰ ት ስ ልጣን ምንጭና ባ ለቤት የሆነው የኢትዮጵ ያ ህዝብ ብቻ ነው።

አና ም ዶ/ር ከሀያ አመት በፊት ሞቶ የተቀበረ አ መለካከት ላ ይ የተቸነከሩ ፖለቲከኞች

ሰለባ ሆነውና እርሰዎም ዛሬ በተራዎ ሌሎችን ሰለባ ለማድረግ ክፉኛ የተጠናወትወ አባዜ“

በሃይል፣በአመጽና በሁከት መንግስት እገለብጣለሁ” ቢያስብሎዎ ትም፣ ይህን የማይመስል

ነገር በሚቃዡበት አገር የቅዠ ትዎ ተጋሪ ከሆኑ ሰ ዎች ከሚሰበሰ ብ ገንዘብ ላይ ዳረጎት

ያገኙበት እንደሆነ እንጂ ማንም እንደማይሰማዎ ት ቢገነዘቡ ብልህ ነት ነው ።